# ኩንስንሱ ጳጳስ

ከእኔ ዓለም

የሃገረ ቅድስት ማዕረግ ተችሯቸው
ጳጳስ ሆነው ሳለ ክብር ተሰጥቷቸው
ፖለቲካ ወደው ዓለማዊ ኑሮ ተፈታተናቸው
የያዘ አብዜ መቼም አልተዋቸው
እኝህ ብርቱ ካህን ኃጢአት ደሞዛቸው
ንስኃ ሳይገቡ እንደናፈቃቸው
ስንቅ ነብስ የሚሆን ምግባር ሳይኖራቸው
መስቀሉን አንግተው ሞት አስቀደማቸው
የአክሱሙ እጨጌ ቀረ መንበራቸው
ኩንስንሱ ጳጳስ ወይ አሟሟታቸው።

- 

# ጠቢቡና ሊቁ

በአገሬ ኢትዮጵያ ጉድ ተሰማ ወሬ
የታማው አልቀረ እውን ሆነ ዛሬ
ሰውዬው ታመመ ብለው ቢነግሯቸው
ሽቅብና ቁልቁል ድንገት ጀመራቸው
ሞትኮ ዓለም ነው አይ አካሄዳቸው
መብረክረክ ጀመረ ፍርግርጉ አልጋቸው
ከቁንጮው ተነሳ ወይ መጨረሻቸው
ቀሪዎቹን አሰብኩ ምን ይሆን እጣቸው?
ጠቢቡና ሊቁ ብዙ ያነበቡ
ተከታትለው ሄዱ እየተሳሳቡ
ከነኃጢታቸው ንሳኃ ሳይገቡ።